እንደ የሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የ SBIRT መርሃ ግብር መጀመሪያው ክፍል፣ **(insert school name)** የራስህን ፈትሽ ማጣርያ(Check Yourself screener ) ለተማሪዎች ይሰጣል። የ SBIRT የመከላከል ተነሳሽነት ዓላማ የወጣቶች የአደንዛዥ ዕጽ አጠቃቀም ለመቀነስ፣የአእምሮ ጤንነት ለማሻሻል፣እና ተማሪዎችን ለመበልፀግ ከሚያስፈልጓቸው ግብዓቶች ለማገናኘት ነው። ተማሪዎች በ SBIRT ፕሮግራም በሚሳተፉበት ጊዜ በተከታታይ የዳሰሳ ጥናቶች ጭምር ሊሳተፉ ይችላሉ።

በራስህን ፈትሽ ማጣርይ(Check Yourself screener ) እና በተከታታይ የዳሰሳ ጥናት ላይ የሚደረግ ተሳትፎ ሙሉ በሙሉ በፈቃደኝነት የተመሰረተ ነው::ቤተሰቦች ለተማሪዎቻቸው ላያሳትፉ ይችላሉ፣ተማሪዎችም ጭምር መሳተፍ አልፈልግም ሊሉ ይችላሉ። ላለመሳተፍ የሚያስቀጣ ቅጣት የለም እናም በተማሪዎ ውጤት ላይ ምንም ተፅእኖ የለውም። የማጣርያው እና ተከታታይ የዳሰሳ ጥናቱን ቅድመ እይታ ለማግኘት ለሚፈልጉ የ **(insert school name)** ቤተሰቦች ቅጂ ይገኛል። በማጣርያው/በዳሰሳ ጥናቱ ላይ ቅድመ ዕይታ ማከናወን ወይ ተማሪዎን ከዚህ ተሳትፎ ለማስወጣት ከፈለጉ እባክዎ(**insert name, email, telephone number**) ያነጋግሩ።

ስለ SBIRT ወይም ስለ ራስህን ፈትሽ የበለጠ መረጃ ለማግኘት ከዚህ በታች ያሉት በተደጋጋሚ የሚነሱትን ጥያቄዎች ይመልከቱ::ስለ SBIRT ከሆነ ሰው ጋር ለመነጋገር ከፈለጉ እባክዎ (**insert name, email, telephone number )** ን ያነጋግሩ ።

---

**SBIRT እና ራስህን ፈትሽ ምንድን ነው?**

ማጣሪያ(Screening) ፣ አጭር ጣልቃገብነት (Brief Intervention) እና ወደ እንክብካቤ መላክ( Referral to Treatment) (SBIRT) የእፅ አጠቃቀምን ለመለየት ፣ ለመቀነስ እና ለመከላከል  እና የአእምሮ ጤናን ለማሳደግ ጥቅም ላይ ይውላሉ::

የሲያትል የህዝብ ት/ቤቶች   SBIRT መርሃ ግብር በ King County's Best Starts for Kids initiative የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግለት ሆኖ ጤናማ እና ጠንካራ የሆኑ ሕፃናት፣ ወጣቶች፣ ቤተሰቦች እና ማኅበረሰቦች ለመፍጠር መዋእለ ነዋዩ ኢንቨስት የሚያደርግ መርሃ ግብር ነው። SBIRT ሶስት ዋና ዋና ክፍሎች አሉት::

- ***ማጣሪያ* (S**creening): ተማሪዎች ስለ ግላዊ የጤና ባህሪያት ፈጣን ግብረመልስ የሚሰጥ አሳታፊ እና ምቹ የሆነ ማጣሪያ(ራስህ ፈትሽ)የወስዳሉ::ደህንነቱ የተጠበቀ ፣ በድር ላይ የተመሠረተ የዳሰሳ ጥናት በማንኛውም የኤሌክትሮኒክ መሣሪያ ላይ ሊከናወን ይችላል።
- ***አጭር ጣልቃ ገብነት*** (**B**rief **I**ntervention): ማጣርያው አስፈላጊ መሆኑን ካሳየ ፣ በተማሪው ጥንካሬ እና ችሎታ ላይ ያተኮሩ ከ ሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ሰራተኞች ጋር አጭር ውይይት ማድረግ።
- ***ወደ አገልግሎቶች መላክ*** (**R**eferral **T**o services): ተማሪው ተጨማሪ ድጋፍ የሚያስፈልገው ከሆነ፣የሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ሰራተኞች፣ ለተማሪዎች/ቤተሰቦች ፍላጎታቸውን መሰረት ያደረገ ልዩ አገልግሎት ወደሚያገኙበት ይመራቸዋል።

***ራስህ ፈትሽ ማጣራያ*** በዋሽንግተን ዩኒቨርስቲ የሲያትል የህፃናት ሆስፒታል የሚዘጋጅ፣አሳታፊ የሆነ፣ተማሪዎች በ SBIRT ፕሮግራም ውስጥ ሊሳተፉ የሚችሉበት ምርምር ላይ የተመሰረተ መሳሪያ ነው። የኪንግ ካውንቲ ወጣቶች እና ወላጆች በዚህ መሣሪያ እድገት ላይ ተሳትፈዋል፣እና ግብረመልሶቻቸው ግልፅ የሆነ ፣ ባህላዊ ምላሽ ሰጪ እና ለወጣቶች ተስማሚ የሆነ ማጣሪያን በማጠናቀር ረገድ በጣም አስፈላጊ ነበር። የመሳሪያው ግብ ተጨማሪ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ወጣቶችን ለመለየት እና ተማሪዎች ጤናማ ምርጫዎችን እንዲያደርጉ የሚያበረታታ  በተማሪዎች እና በትምህርት ቤቶቻቸው ድጋፍ ሰጪ ቡድን ጋር ውይይት እንዲደረግ ለማገዝ ነው::ይህ ሞዴል በዋና የጤና ተንከባካቢ ጤና ጣብያዎች ፣ በትምህርት ቤት ላይ የተመሰረቱ የጤና ክሊኒኮች እና የድንገተኛ ጊዜ ክፍሎች ግለሰቦችን በመርዳት ረገድ ስኬታማ መሆኑ ተረጋግጠዋሉ።

Amharic

**በዚህ በፕሮጀክቱ ውስጥ የሚሳተፉ የሲያትል ትምህርት ቤቶች የትኞቹ ናቸው?**

Eckstein መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ፣Hamilton International መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣Jane Addams መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ፣Madison መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ፣Meany መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ፣Whitman መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣እና Seattle World ትምህርት ቤት በአሁኑ ጊዜ የ SBIRT ፕሮግራም ተግባራዊ ያደርጋሉ።እነዚህ ሰባት ትምህርት ቤቶች በየሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች መከላከል እና ጣልቃ ገብነት መርሃ ግብር ድጋፍ፣በ BSK SBIRT የገንዘብ ድጋፍ ጊዜ ሁለንተናዊ የ SBIRT አገልግሎቶችን ይሰጣሉ።በ 2021-2022 የትምህርት ዓመት ተጨማሪ ሁለተኛ ደረጃ ት / ቤቶች የ SBIRT የሙከራ መርሃ ግብር ሊካይዱ ይችላሉ።

**ራስህ ፈትሽ ማጣርያ አማራጭ ነው?**

አዎ! የራስህ ፈትሽ ማጣራይ እና ሁሉም ሌሎች የ SBIRT ክፍሎች ለመሳተፍ በፈቃደኝነት ነው:: የሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ሰራተኞ ስለ SBIRT እና ስለ ራስህ ፈትሽ ማጣርይ ለተመረጡ ተማሪዎች ያስተዋውቃሉ፣የማጣራያው ተፈጥሮ እና ምክንያት ያብራራሉ፣እና ለመሳተፍ ፈቃደኞች ከሆኑ ይጠይቋቸው። ተማሪው ለመሳተፍ ከመረጠ፣ የሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ሰራተኞች እነሱ የሚጠቀሙትን የማጣሪያ መሳሪያ ይሰጧቸዋል። በተጨማሪ፣ በማጣሪያው ላይ ያለው የመጀመሪያው ጥያቄ ተማሪዎች ለመሳተፍ መስማማታቸውን ይጠይቃቸዋል። ላለመሳተፍ ከመረጡ(ስምምነት ላለመስጠት ከመረጡ)፣ከዚያም ማጣርያው ይጠናቀቃል። ወላጆች / አሳዳጊዎች የትምህርት ቤታቸውን አስተዳደር፣የአማካሪ ቡድኑ፣ወይም የ SBIRT ሰራተኛን በማነጋገር ልጃቸውን ላለመሳተፍ ማድረግ ይችላሉ ::

**የራስህን ፈትሽ ማጣርያ(Check Yourself screener)የሚወስዱ ተማሪዎች የትኞቹ ናቸው?**

የራስህን ፈትሽ ማጣርያ(Check Yourself screener )ለሁለቱም ለሁሉም እና ለተመረጡ ተማሪዎች ይሰጣል። ሁሉም ሰባቱ የ SBIRT መካከለኛ ደረጃ ት / ቤቶች በተወሰነ የክፍል ደረጃ ላሉ ብቁ ለሆኑ ተማሪዎች ሁለንተናዊ ማጣርያን(universal screening )ይሰጣሉ :: ሦስቱ የሙከራ ትምህርት ቤቶች ለአነስተኛ የተማሪ ቡድኖች ማጣርያዉን ይሰጣሉ። ሁለንተናዊ ማጣሪያ ትምህርት ቤቶች ትልልቅ ጉዳዮች ከመከሰታቸው በፊት በቀላሉ ሊፈቱ የሚችሉ ችግሮችን ቀደም ብሎ ለመለየት ያስችላቸዋል። በተጨማሪም ፣ የተመረጡ ተማሪዎች የራስህን ፈትሽ ማጣርያ(Check Yourself screener )እንዲወስዱ ይጠየቃሉ። ለዚሁ ማጣርያ የሚመረጡ ተማሪዎች ራሳቸው ከመረጡ፣ዝቅተኛ አቴንድንስ ፣ንጥረ ነገር በመውሰድ የሥነምግባር እርምጃዎች፣ወይም ሌሎች ተጨባጭ የተማሪ መረጃ ምንጮች መሰረት በማድረግ ነው።

**በማጣሪያው ላይ ምን ይጠየቃል?**

ራስህ ፈትሽ ማጣርያ የጥያቄዎቹ ቁጥር እና ዓይነት በተማሪ መልሶች መሰረት የሚለያዩ ኢንተራክቲቭ የሆነ መሳርያ ነው። አብዛኛውን ጊዜ ወደ 40 የሚጠጉ ጥያቄዎች ይጠየቃሉ፣ እና አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ማጣራያውን ለማጠናቀቅ ከ10-15 ደቂቃዎች ያህል ይወስዳሉ።ጥያቄዎቹ ስለ ስነ-ሕዝብ፣ ጥንካሬዎች፣ ድጋፎች፣ ግቦች፣ የአደንዛዥ እጽ አጠቃቀም፣ የአዕምሮ ጤና፣ ጉዳት እና ደህንነትን በተመለከተ ይጠይቃሉ።

**የማጣሪያ ውጤቶች ማን ያያቸዋል?**

ማጣሪያው በትምህርት ቤቱ የመከላከያ እና ጣልቃ ገብነት ባለሞያ የሚካሄድ ሲሆን፣ እና የተማሪ ውጤቶችን እንደአስፈላጊነቱ እንደ አማካሪዎች ወይም ነርሶች የመሳሰሉ አግባብነት ያላቸው የሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ሰራተኞች ሊታዩ ይችላሉ። ተማሪዎች ማጣርያ ሲወስዱ proxy ID የጠቀማሉ ፣ የተማሪ ስሞች ወይም የሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የተማሪ ቁጥሮች አይገቡም። ውጤቶቹ አንድ ተማሪ ስኬታማ ለመሆን የሚያስፈልጉትን ድጋፎች ለመወሰን የሚያግዙ ጠቃሚ ግብረመልስ ይሰጣሉ። የተማሪ የማጣራያ ውጤት ከ ሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ሰራተኛ ውጭ ለመስጠት ከተጠየቀ፣ውጤቱ ይፋ ከማድረጉ በፊት በ FERPA በኩል በሚወጣ ፎርም ከወላጁ /አሳዳጊ የጽሑፍ ፈቃድ ቅድምያ መገኘት አለበት።

**ወላጆች /አሳዳጊዎች ስለ የራስህን ፈትሽ ማጣርያ(Check Yourself screener )እና ስለ SBIRT ፕሮግራም እንዴት ይነገራቸዋል?**

እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ከሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች የትምህርት ቦርድ ፖሊሲዎች እና ተግባራዊ ከሚሆኑ ህጎች ጋር የሚስማማ የራሱን የሆነ የወላጅ ተሳትፎ እቅድ ያዳብራል እና ተግባር ላይ ያውላል።የ SBIRT የወላጅ ተሳትፎ እንቅስቃሴዎች በስርዓተ ትምህርት ምሽቶች ፣ በወላጅ የትምህርት ዝግጅቶች ፣ እና በት / ቤት እና በ SPS ድርጣቢያዎች ላይ የሚለጠፉ መረጃዎች ያካትታሉ :: በተጨማሪ ወላጆች \አስዳጊዎች እንደ የትምህርት መጀመርያ አካል በትምህርት ዓመቱ መጀመሪያ ላይ ለሁሉም ተማሪዎች በሚሰጠውን ጥቅል ላይ ፕሮግራሙን በተመለከተ ቀጥተኛ የጽሑፍ ማስታወቂያ ይቀበላሉ። ወላጆች/ አሳዳጊዎች የወጣቶች ጤና የዳሰሳ ጥናት ጥያቄዎችን ለመገምገም ከሚደረገው አሰራር ጋር በተመሳሳይ መልኩ ከጠየቁ የራስህን ፈትሽ መሳሪያ መገምገም ይችላሉ።በተጨማሪም ፣ የልጃቸው ማጣርያ ከፍተኛ አደጋን የሚያመለክት ከሆነ ወላጆች/አሳዳጊዎች ይነገራቸዋል።